


# Lessings Ringparabel



# Nathan der Weiſe.

Ein

Dramatiſches Gedicht,

in fünf Aufzügen.

Jntroite, nam et heic Dii ſunt!

APVD GELLIVM.

Von

Gotthold Ephraim Leſſing.

1779.

[…]

## ትዕይንት 4

## በሳላዲን ቤተ መንግሥት አዳራሽ (ችሎት)
## ሳላዲንና ሲታ

| | |
|---|---|
| ሳላዲን | (አመራር እየሰጠ ነው) |
| | ያ አይሁዳዊ እንደመጣ ወይኔ ባፋጠኝ ሳነሁት |
| | እጅግ በጣም ተንቀርፍፎኛል ወዲህ በቶሎ እንደመምጣት |
| ሲታ | አይመስለኝም ሳላዲን |
| | ቤቱ ሄደው ሲፈልጉት |
| | አጥተውት ይሆናል ምናልባት |
| ሳላዲን | ኸረ ተይኝ ጀል እት ዓለም ! |
| ሲታ | ምነው አጣዳፊ ጦርነት ያለብን አስመሰልከው |
| ሳላዲን | እኮ ሲታ ! ነው እንጂ ! ጦርነትማ ነው ያለብኝ |
| | ያውም እጄ ባልለመደው መሣሪያ ልዋጋ ነኝ |
| | ታዲያ እንዲህ ባለው ጊዜ፡ አስመሳይ ሁን ነው እምትይኝ |
| | ጥንቃቄ፡ የአይጥ ወጥመድ፡ ጠምዶ ማድባት አለብኝ? |
| | ይህን መሰ ተማርኩና |
| | ለምንስ ጥቅምና ዓላማ እስከዛሬ ሲያሀልቀኝ ጣና? |
| | ለገንዘብ ለብር ብዬ፡ ለአፍኛ ማግኛ ልመና ! |
| | ሲያውም ከአንድ አይሁዳዊ እጅ፡ ልለነስ ገና ለገና ! |
| | እንዲህ ወዳለ ወራዳ፡ ተራ ተርታ የወረደት ማጥ |
| | እኔ ሳላዲን ልዘቅጥ ? |
| | የርካሽ ርካሽ ግም ነገር |
| | አገኝ ብዬ በሎሌነት፡ ለባለጌ ዘዴ ላድር ! |
| ሲታ | ግን ርካሽም ነገር፡ እጅግ በተናቀ ቁጥር |
| | ይገኛል እኮ ውሎ አድሮ፡ የራሱን ዘቀል ሲፈጥር |
| ሳላዲን | እሱስ እውነት ነው ልክ ነው ! |
| | ግን እሺ ይሄ አይሁዳዊ፡ ያኔ ደርበሾ እንደቀባው |
| | ርቱዕ፡ ብልኅና መልካም ሰው |
| | ሆኖ በስሉ ብናገኘው |
| | እኮ ምን ሊኮን፡ ሊባል ነው ? |
| ሲታ | ያኔማ አረፍክ በቃ |
| | ችግርህም ሁሉ አበቃ |

ምክንያቱም ወጥመድ ያልከው
በእንድምታ የሚጠቁመው
አያሁዱ ተጠማጅ አውሬ ፤ እባይ ሌባ መሆኑን ነው
እንጂ ርቱዕ መልካምነት፣ በዘሩ የለም ማለት ነው
ርቱዕ ሰው ነው ካልን ግን ወጥመድ ሳያሸን አቀፍነው
የኛው ገንዘብ አደረግነው
እንዲህ ያለም ሰው ሲናገር ማዳመጥ ደስታችን ነው
እሊያም ልቡ–ጥኑ ሆኖ፣
በጥንካሬው ተማምኖ
እስረህ የዘረጋኸውን ሴራ የወጥመድ መረብ በትኖ
እንዴት እንደሚያመልጥህም፣ ዘዴ መላውን አጢኖ
ማየትም ቢሆን ደስታ ነው
አበክሮ ለሚያየው ሰው

ሳሳዲን — ትክክል ነሽ ሲታዬ !
ታይቶ እማይታወቅ ፈሽታ የሚያመጣልኝ ነገር ነው

ሲታ — እንግዲያስ ምን አስጨነቀህ ?
እንደሌሎቹ ዘሮቹ፣ እሱም ቀጣፊ ከሆነም
ሊታፍር አይገባህም
ሌሎቹን ሰዎች እንደሚያይ፣ አይቶ ነው የሚያገኝህም

ሳሳዲን — ወቸ ጉድ ! ብልኅነትን ለሴት ልጅ ከነሽሩኑ መስጠቱ ?…

ሲታ — እንዴት ከነሽሩኑ ?
እረ ወይኔ ወንድምዓለም፣ በራስህ ድፍረትን አስና
አንተ ፍቃዱ ይኑርህ፣ ለሌላው እኔ እሰሁና
ድልን የተጎናፀፍኩት በሃይሌ ብቻ ነው ማለት
ካንተ እያነት ሰው እማልጠብቀው
የሚያስገርመኝ ነገር ነው

ሳሳዲን — እኔ ደሞ እሚያስገርመኝ፣ የሴቶች ሁሉ ደስታቸው
ወንዶችን እንደየአቅማቸው
ስበው ጉትተው አውርደው
መድበው ማስቀመጣቸው
ብዙ ሂዷልኝ ሲታዬ ትምርትሽ በደንብ ገብቶኛል
ደሞ አውቂ ተጠንቀቂ
በሚስጥር ለማዳመጥ እዚህ እንዳትደበቂ
አይሻለሁ ልብ አድርጊ.
(ሲታ ወንደኛው በር ስትወጣ ናትናኤል በሌላኛው ይገባል ሳሳዲን ይቀመጣል)

# ትዕይንት 5

## ሳላዲንና ናትናኤል

| | |
|---|---|
| ሳላዲን | ና ቅረበኝ አንት አይሁድ |
| | ና ፍርሃትህን አስወግድ |
| ናትናኤል | ፍርሃትማ፡ ሱልጣን ሆይ |
| | የእርስዎ ጠላቶች ዕጣ ነው |
| ሳላዲን | ስምህ ናትናኤል አይደል ! |
| ናትናኤል | አዎ ሡልጣን ሆይ |
| ሳላዲን | እኮ ናትናኤል ጠቢቡ |
| ናትናኤል | የለም |
| ሳላዲን | ብቻ ሕዝቡ የሚጠራህ፡ እንደዚሁ እያለ ነው |
| ናትናኤል | ያ ዕውነት ሊሆን ይችላል፤ በሕዝቡ አፃን |
| ሳላዲን | አየህ እኔ የሕዝቡን ድምጽ፡ በጥላቻ አይን አላይም |
| | ስለዚህም ጠቢብ ብሎ፡ ራሱ ያመነበትን ሲሳይም |
| | ማንን እንዳለ ለማወቅ፡ እጓጓለሁ እንጂ አልጠላውም |
| ናትናኤል | ግና ሕዝቡ የሰየመው በፌዝ ለስላቅ ከሆነስ |
| | ጠቢብ ሲል ክፉ ቢሆንስ |
| | ክፉም ማለት ጥቅሙን አውቆ፡ ራሱን ወዳድ ቢሆንስ ? |
| ሳላዲን | እውነተኛ ጥቅሙን የሚያውቅ ማለትህ ይሆን ? |
| ናትናኤል | እንግዲያውስ ሡልጣን ሆይ፡ ክፉ ሰዎች እራስ ወዳድ |
| | መሆናቸው ነው ገሃድ |
| | በዚህ ዓይነት ጠቢብም ሆነ ክፉ |
| | አንድ ሊሆን ነው ማለት ነው፤ ያው በትርጓሜ መስፈሩ |
| ሳላዲን | አንተኮ አሁን ያረጋገጥከው መቃወምህ ያሻህን ነው |
| | የሰው እውነተኛ ጥቅሞች፡ ከቶም ምን ምን መሆናቸው |
| | በሕዝቡ አይታወቅም |
| | ሊያውቃቸውም ግሮ አያውቅም |
| | ይሄ ብቻውን እንግዲህ ሰውን ጠቢብ ለማድረግ |
| | በቂ ሰበብ ይሆነዋል ለመብቃት ለአደባባይ ወግ |
| ናትናኤል | ያ ያማ ማንም ሰው ቢሆን፡ ስለራሱ የሚለው ነው |
| ሳላዲን | የትህትና ምክግ ! |
| | እውነትን ለማግኘት ብለን፡ ደረቅ ምክንያት ስንቆፍር |
| | አድካሚም ጉዞ ተጉዘን ስናገኘው ነው የምንቀር |

(ይነሳል)
ስለዚህ፣ እቅጩን እንነጋገር
ሰማህ አንተ አይሁድ፣ ቀና ሁን
በሚገባም አውጣቸው፣ ግልጽነት ታማኝነትክን

ናትናኤል    ሡልጣን ሆይ ቢበኩሉ፣ እርስዎ ብሎት ሳገለግል
ፍጹም ዝግጁ ነኝ ከቶ ባዘዙኝ አግባብ ልውል

ሳላዲን    እኮ፤ እንዴት ታገለግለኛለህ ?

ናትናኤል    ካለኝ ሁሉ ምርጥ ምርጡን ለርስዎ፣ ልሰጥ ሳገለግል ስወድ
በቀላል ፍቃድዎ ሥር፣ ተጠልዬ ነው እምራመድ

ሳላዲን    ይህን ስትልስ እንዴት ነው ? ሁቤት ንግድህን አዳል ?
እሁቴ አለች ለዚህ ለዚህ፣ ለማስማማት የእኔ ወኪል
(ይሄ ለአዳማጩ ነው)
ንግድ ነክ ነገር ላይ እስከዚህም ነኝ እኔ
ንግድን በሚመለከትም፣ ምንም ቃኝቶ አያቅም ዓይኔ

ናትናኤል    ያለጥርጥር ግን በእርግጥ፣ አግረ መንገዴን ስዟዟር
የጠላትን ጉዞ እቅጣጫ፣ አይቼ እንደሁ ስልቱን ጭምር
መቼም መጠየቅሁ አይቀር ?
ያድፍጥም ይንቀሳቀስም
ማወቅ መፈለጉ አይቀርም ?
እና የኔን ግምት ካሉኝ

ሳላዲን    ያም አይደለም የኔ ጉዳይ፣ እሱን በበቂ አውቀዋለሁ
ብቻ አድምጠኝ እነግርሃለሁ

ናትናኤል    ታዛዥ ነኝ

ሳላዲን    እንግዲህ አንተም ብትሆን፣ ጠቢብ ነህ ብለዋልና
የቱ እምነት ወይም ሕገ ደንብ፣ እንደሚበጅ ሆኖ ዋና
ትነግረኛለህ ታስብና

ናትናኤል    ሡልጣን ሆይ እኔኮ አይሁዳዊ ነኝ

ሳላዲን    እሱማ እኔም እስላም ነኝ
በመሀከላችን ደግሞ ክርስቲያኑ ነው የሚገኝ
እንግዲህ ሶስቱ ሀይማኖቶች፣ ፊታችን ተደቅነዋል
ከነዚህም ሁሉ ደግሞ፣ አንዱ ነው እውነት ትክክል
መቼም እንዳንተ ያለ ጠቢብ፣ በውልደቱ ገጠመኝ ስም
ይህ ነው እምነትህ ቢሉት፣ እሺ ብሎ አይቀበልም
አሊያም ቢቀበል እንኳ፣ የሚመርጥበት ምክንያት
ይህን ከዚያ አወዳድሮ፣ የሚያጤንበት ሥርዓት

እንዱን የተሻለ ብሎም፣ የመወሰኑ ክህሎት
በረቂቅ አስተሳሰቡ፣ በአእምሮው ሚዛን ጋሻነት
የሚደገፍ ነው ብዬ ነው፡ እኔ በእውነት የምገምት
ታዲያሳ ጌታ ናትናኤል፣ እስቲ ካንተው ልስማ ኪኑን
ያንተን ሃይማኖት ምርጫህን፣ በውል የለኩህበትን
እኔ በቂ ጊዜ አግኝቼ፡ መርምሬ የማላጣውቀውን ።
መቼም ቀዳሚው ሡልጣን ነኝ፣ በእንዲህ ያለ አጉል ድፍረት
የማይነሳውን ጉዳይ፡ በይፋ ውስጡን ለማውራት
ምናልባት የመጀመሪያው ብሆንም ይግሞ አላፍርበት
ለነገሩ አይታየኝም፣ ማንም ሡልጣን የሚያፍርበት
የመጀመሪያው ነኝ በእርግጥ ?
እንዴ… በል አንጂ ተናገር
ነው ወይስ ብትን ሀሳብክን፣ ለመሰብሰብ ጊዜ ፈለግህ
አስብበት ደስ ይለኛል፣ ብትመልስ ጊዜ ወስደህ
(ጉንኛ) ያልኩትን ትሰማ ይሆን ?
ይሄኔ ትነግረኝ ነበር፣ ትክክል ሰርቼ እንደሆን
ካለች ልቀበላ ምክሯን)
በል አስብና ንገረኝ
ቶሎ ነው የምመለሰው፣ መጣሁ እያብላላህ ቆየኝ
(ይወጣል)

## ትዕይንት 6

## (ናትናኤል ብቻውን)

ናትናኤል

የሚገርም ነገር እኮ ነው ! ይሄ ምን ሊሆን ይችላል ?
ሡልጣን ከእ ምን ይሻሉ ? ለምን ግራ ያጋቡኛል ?
እኔ የመጣሁ ለገንዘብ፡ እሳቸው እውነት ይሻሉ !
እውነት ! አዎን እውነት !
ዕውነትን ነው እሚፈልጉት
ምን ነካቸው ?
ዕውነት ገንዘብ መሰላቸው !
ሀቅ ሀቅ የሚያሰኛው
ሀቅ መሀለቅ መሰላቸው
እንደ መርቅስ ቢያከማቹት

በከረጢት ጳጥረው ይዘው፣ ለክፉ ቀንስ ቢያኖሩት
ጠቢብ ጭንቅላት ከገዢና ውስጥ፣ ሊኖር ይችላል ወይ እውነት ?
እስቲ በጥቂ እንተረድ ፣ አይሁዳዊው እውን ማነው ?
እውነትን ነው እምሻ እሚሉ፣ ዕውን ዕውነት ቸገራቸው ?
አሁን እውነት ነው ግባቸው፣ እውነትስ ነው እላማቸው ?
ወይስ የስውር ወጥመድ አፍ፣ መሠሪነት መሆኑ ነው ?
ለሳቸው ክቡር አዕምሮ፣ ይህ መቼም ትንሽነት ነው
ጻሩ ትንሽነትስ፣ ታላቅ ለሆነ ምን ነው
ለሚፈለገው ግብ መምቻ፣ ሁሉ ትንሹ ሲጠቅመው ?
ለነገሩስ በዚያ ፍጥነት ለምን እቤት ፈጥነው ገቡ
እንደወዳጅ እንኳ ቢሆን፣ ቆሞ ማንኳኳት ነው ደንቡ ?
መጠንቀቅ ነው በቃ ደጉ
ያም ሆኖ አሁን ተገፍቶ፣ እንደግብር አይሁድ መሆን
የማያዋጣ መንገድ አይሆን
አይሁድነቴንም ገፍቶ ጭራሽ መተው ከቶ አያድን
ምክንያቱም አይሁድ ካልሆንኩ፣ ለምንስ እስላም አትሆን
የሚል ጥያቄ ያስነሳል
እውን አሁን መላው ታየኝ፣... ተረት ብነግራቸው ይሻላል
አዋቂም ሰው እንደሕጻን፣ ተረት ሲነግሩት ጭጭ ይላል !

## ትዕይንት 7

## ሳላዲን እና ናትናኤል

ሳላዲን — (በጉንኛ) ስጡት ድርሻውን ግልጽ ነው ያሁ !
በጣም አልፈጠንኩም አይደል !
አስብክበት ናትናኤል ?
በል ንገረኝ ! ማንም አይሰማም አይዞህ ጸል።

ናትናኤል — ኧረ ዓለም ቢሰማው ነው ሚሻል !

ሳላዲን — ስለ ዓላማ ምክንያትህ
ይሄን ያህል እምነት አለህ ?
እርግጥ አንዳች ጠብታ ዕውነት፣ መደበቅ ብልኅነት ነው
ምክንያቱም እውነት ለችግርም፣ ለሕይወት ለዕቃም ነው ፋይዳው

ናትናኤል — እሱስ ጥቅም ሲሰጥና የሚያተርፈንም ሲሆን ነው

ሳላዲን — እንግዲያውስ ካሁን ወዲያ፣ ከስሞቹ ሁንዱ ይቀናኝ

"ዓለምንና ሕጎቿን ፥ ሊዋጬ ሰው !" እንዳያሰኘኝ

**ናትናኤል** በእውነት ክብር ስም ነው ይሄስ
ግና ሡልጣን ሆይ ንገሬን፥ ከማስረዳቱ አስቀድሜ
አንድ ታሪክ ላውጋ ባከም፤ ከዚሁ ጋር አጣጥሜ

**ሳላዲን** እንዴታ !
እኔኮ ተረት ወዳድ ነኝ ፥
ደህና አድርገው ከነገሩኝ።

**ናትናኤል** ደህና አድርገው ! ኦ ሡልጣን ሆይ !
ያማ ሌላ ጉዳይ ነው

**ሳላዲን** ምን ! አሁንም በኩራት አሽቶህ
ትህትናን ታበዛለህ ?
ብቻ ጀምር

**ናትናኤል** ጥንት ከአመታት በፊት፥ በምሥራቅ ግዛቶች ክልል
ከሀብታም ወዳጁ በውርስ፥ ዋጋው ያልተለካ በውል
አንድ ቀለበት ያገኘ፥ ይኖር ነበር አንድ ጉብል
እፁብ የነበረ ደንጊያ፥ እንፀባራቂ ቀለም ያለው
ድምፃም የአስማት ተሰጥኦን፥ የሚያጎናፅፍ ሳረገው
በዚህ ኃይልም ለሚያምን ሰው፥ ፀጋ ስራው ያምላክ የሰው።
ደሀ ምሥራቃዊ ሰው እንግዲህ፥ ይህን ቀለበት ከጣቱ
ለማያ ገባት መሬት ከፍ ቢል፥ በፍጹም አለማውጣቱ
አያስገርምም ምክንያቱ
እንዲያውም ከነዘርሱ አያወጣውም ነበር፥
እሱም በዚሁ ኃይሉ አስባብ፥ የቤቱም ጌታ ነው ብርቱ
ውሉ አድርጎ ግን ለሚወደው፥ ለአንደኛው ልጁ አወረሰው
በውርሱም ወቅት ቃል አስገባው
እሱም ማውረስ የሚገባው፥ ከልጆቹ ማህል ለአንደኛው
እንደሚሆን አስጠንቅቆ፥ ሰጠው በተግባር እንዲያውል
ያም የቤቱ ጌታ በተወዳጅ ልጅነቱ
ይዞ ማስተዳደር ያዘ፥ እንደግሉ እንደዕምነቱ
በኃይሉ በቀለበቱ። እያዳመጥከኝ ነው ሡልጣን ?

**ሳላዲን** ገብቶኛል። ቀጥል።

**ናትናኤል** ለልጅ ልጅም ተላለፎ፥ ከትውልድ ትውልድ ተዋርሶ
በመሀከል ለአንድ ልጁ፥ ሶስት ልጆች ላሉት ደርሶ
አንድ ችግር ተፈጠረ
ይሄኛው አባት እንደ ዕድል

ሶስቱንም ልጆቹን እኩል
ሳያደላ ይወዳል
እነሱም እንደአባታቸው
እኩል ጥልቅ ነው ፍቅራቸው
አባት ለመራሽ ልጆቹ፣ ቀለበቱን ሊያወርሳቸው
ለእያንዳንዳቸው ቃል ገባ። ግን ዘንየ ሳይሰጣቸው
በዚህም ጥቂት አመታት፣ ያለውርስ አለፈባቸው
ሆኖም ሞቱ ተቃረበ፣ ሃሳብ ቆንጥጦት እንደዚሁም
ቀለበቱን ለአንዱ አውርሶ፣ ሁለቱ እንዲያዝኑ አይሻም
ሀፍረቱን መሸከሙንም ቍራኙን አልፈለገውም
ምን ያድርግ እንግዲህ ይህ ሰው ?…
ዘዴ አገኘ፣ በመካያው
በምሥጢር ላንድ ወርቅ ሠሪ አንድ ሥውር ትዕዛዝ ሰጠው
ልክ ያንን ወርቅ የመሰለ ምንም የማይለይ በአይነት
የተከፈለው ተከፍሎ፣ ሌላ ሁለት ቀለበት
ተስማምቶ እንዲሠራለት ።
ባለእጁም ቁርጥ ያንኑ፣ የሚመስሉ አበጀለት
እራሱ አባትዬው እንኳ፣ ኖሙኖዋን አውቆ ለማውጣት
አቃተው ባይኑ መለየት
በደስታ ተጥለቅልቆ፣ ያው ሶስቱንም በየተራ
ለብቻ ወስዶ እየጠራ
ቀለበቶቹን አውርሶ ፡ መርቆ አሰናበታቸው
ሕይወቱም አለፈ በዚያው።
ያዳምጡኸል ሡልጣን !

ሳላዲን (ግራ ተጋብቶ ፊቱን አንደዞረ)
እንዴ ! አዳምጣለሁ። በል አጠቃል ተረቱን

ናትናኤል ተረቱማ አልቋል ሡልጣን !
ከዚያ አሚቀጥለው ደግሞ የሚጠይቅ ነው ግምትን ።
አፈር ተመልሶም ሳይደርቅ ገና አባት ከመሞቱ
የቤቱ ጌታ ነኝ አለ፣ ሁሉም ከነቀለበቱ
የጭቃቂ፣ የክርክር፣ የአምባጓሮና የሙግት
መዓት ፈላ ነዲድ እሳት
ግና ሁሉም ከንቱ ነበር፣ ምክንያቱም እውነተኛው
ቀለበት አልተገኘም ያው ---
(ለጥቂት ጊዜ አቆመና የሡልጣኑን መልስ ጠብቆ)

| | |
|---|---|
| | እንደኛው የዕምነት ጥያቄ፣ ይህን ሀይማኖት ከዛኛው |
| | የማወዳደር ዓይነት ነው |
| ሳላዲን | ለኔ ጥያቄ መልስ፣ ይሄው ነው ማለት ነው ያለህ ? |
| ናትናኤል | የለም። |
| | እንደይቅርታ ጥያቄ፣ ያገለግላል ብዬ ነው |
| | ምክንያቱም አባትየው፣ በጥድፊያ እዞ እንዳሠራቸው |
| | ተመሳሳይ ቀለበቶች፣ አንዱን ከሌላው እንዳይለዩዋቸው |
| | እኔም በማምት ባዝን፣ አንዱን ሃይማኖት ከአንደኛው |
| | ሊለየይ ብዬ መታገል |
| | ከንቱ ድካም ይመስለኛል |
| ሳላዲን | ቀለበት አልክ ናትናኤል ! |
| | ታወዳድርልኛለህ ቀለበትን ከእምነት እኩል ? |
| | እኔኮ ያቀረብኩልህ ሃይማኖቶቹ በሙሉ |
| | ከመልበስ መብላት መጠጣት፣ ጀምሮ ይለያያሉ |
| ናትናኤል | አዎን እሱስ ትክክል ነው ! |
| | ከሥር- መሠረታቸው ግን፣ ሁሉም ቢሆን አንድ ናቸው |
| | በጽሑፍ ወይ በአፍ ባህልም |
| | ሁሉስ መሠረታቸውን በታሪክ ላይ አልተከሉም ? |
| | ታሪክ ደግሞ ስንቀበል፣ መታመን አለበት መቸም |
| | አይደለም እንዴ ? |
| | ለመሆኑ በማን ላይ ነው |
| | ብዙ ትጅ እምነት የምንጥለው ? |
| | በራሳችን ሕዝቦች ላይ ነው ! |
| | የደም አጥንት ወርሳችንን፣ ያገኘንበትን ሰዎች ? |
| | ሳይዋሹን በእውነት እንዋረው |
| | መዋሸታቸው ለኛ ጥቅም፣ ብለው ካልሆነ በቀር |
| | ከልጅነት ዕድሜ እንስተው |
| | በፍቅር እንቀልባ አሙቀው ። |
| | እርስዎ ለርሶ ቅድመ አያቶች፣ ከሚሰጡት ዋጋ ቢታች |
| | ለምን ዋጋ እጐሳለሁኝ፣ እኔስ ለኔ ቅድመ አያቶች ? |
| | ወይ ደግሞ በተቃራኒው፣ የእርሶን ዘሮች ዋሾ ብለው |
| | እንዲጠሩ፣ እኔ ብገፋ፣ የእኔ እንዲታዩ ከፍ ብለው |
| | ለክርስቲያኖችም ይሄው ነው። |
| ሳላዲን | እረ በነቢያችን፣ ይህ ሰው ያለው ልክ ነው |
| | እኔ የለኝም የምለው |

ናትናኤል እስቲ ወደ ታሪካችን፣ ዞረን ደግሞ እንመለስ
እነዚያ ወራሽ ልጆች፣ ሙግት ገጠሙ ብለናል
እያንዳንዱ ልጅ ለዳኛው፣ ስለቤቱ ውርስ ያስረዳል
አባታቸው ምርቃቱን፣ የቀለበቱንም ሥልጣን
እንዳስረከባቸው በግል፣ በዝርዝር ገልጿል እውነቱን
ከዚያም እያንዳንዱ አስረዳ፣ አባቱ እንደማይዋሸው
እንዲህ ያለ ተራ ሽፍጥም፣ በጭራሽ እንደማያውቀው
ደግሞም ምንም ወንድሞቹን፣ መክሰስ ባይፈልግ አንዱ አንዱን
አንድ የተንኮል ሴራ እንዳለ፣ ሁሉም ጠርጥሯል ሌላውን

ሳላዲን እሺ ! ታዲያ ዳኛውስ ምን አለ ?
ምን እንደምትል ለማወቅ ፣ እጓጉቶኛል ምን እንዳለ
ቀጥል እሺ ምን አለ ?

ናትናኤል ዳኛውማ ያለው። አባትየው፣ እዚህ መጥቶ፣ ባካል ቀርቦ ካላየሁት
አልችልም ፍርዱን ለመስጠት
ጭራና ቀንድ የሌለውን ጉድ፣ ጭብጥ ብዬ ፍርድ እንድሰጥ
ይታሰባል እንዴ በእርግጥ ?
እውነተኛው ቀለበትስ ምንስ የአስማት ነው ቢባል
አፍ አውጥቶ ይናገራል ?
ግን ቆይ እስቲ አድምጡኝ !
ቀለበቱ ምትሀታዊ ኃይል ይሰጣል ካላችሁኝ
በእግዚሃርም በሰውም ፊት፣ ያስወድዳል እንደሚሉኝ
በትክክል ካስረዳችሁ
እንግዲያውስ ውሳኔውን፣ ለቀለበቱ እተዋለሁ
ከሶስቱ ወንድማማቾች፣ የቱ ተወዳጅ እንደሆን
ይሄ የአስማቱ ቀለበት፣ ይስጠን እንጂ ታዲያ መልሱን ?
እረ የሰማያት ያለህ ! የፍቅር ቀለበቶቹ እንዴት ነው ጥምር
ሥራቸው
ውስጥ ውስጡን ማብላላት እንጂ፣ ወደውጭ አይዘልቅ ኃይላቸው ?
እያንዳንዱ ለየራስ ነው
ፍቅር ጦሩን የሚሰብቀው ?
እናንተ እንግዲህ ሁላችሁ
ተታላይ አታላይ ናችሁ።
ቀለበቶቻችሁም ሁሉ፣ የሀሰት ናቸው የድልል
እውነተኛዋ ቀለበት፣ ምናልባት ድራሿ ጠፍቷል
አባታችሁ በምትኳም፣ ሶስት አዳዲስ ወርቆች ገዝቷል

ሳላዲን	በጣም ግሩም ! በጣም ግሩም ድንቅ ነው !

ናትናኤል	ዳኛውም በመቀጠል፦
ግን ፍርድ እንዲሰጣችሁ ፤ እጅጉን ካመረራችሁ
የእኔንም ምክርና ሃሳብ፡ እንፈልገውም ካላችሁ
ይሁን ይሁንላችሁ ። የነገሩን ልቡን እዩ
እያንዳንዱ ልጅ ከአባቱ፡ ወርቅ አግኝቷል ልዩልዩ
በበኩሌ እየመከርኳችሁ፡
ሁሉም በየፊናው ያስብ፤ ዕውነተኛው የሱ እንደሆን
ምናልባትም አባታችሁ፡ አንዱ ብቻውን እንዳይገን
ሶስት ቦታ ከፍሎት ይሆናል ለመበተን ከቶ ኃይሉን
እያንዳንዳችሁን በየነብስ፡ ያለአድልዎ ያፈቅራችኋል
ስለዚህም ለአንዱ ብቻ፣ ዕጣውን መስጠቱን ጠልቷል
ያን በማድረግ ሁለቶቹን፣ ማስቀየሙን ተረድቶታል
እንግዲህ እያንዳንዳችሁ፡ ይሄንን ፍቅር ውረሱ
ከጥላቻ ነጻ ሁኑ፡ በመንፈስ ቅናት ገስግሱ
በጥረት ተብላለጡ፤ በዚያም የቀለበታችሁን
ምግባረ–ሠናይ በማልማትና አሳዩ መርጋታችሁን
ለዚህ ሁሉ ደግነትን፣ ጸጋውን ልባዊ ፍቅርን
ከአምላካችሁ እምነት ጋራ፣ አዋህዱት ቅን ምግባርን
እናም በሺህ አመታት ውስጥ፣ የቀለበቱም አቅም ኃይል
በአንዳችሁ ዕጣ ላይ ወድቆ ዳግም በውን ነብስ ይዘራል
የልጅ ልጆቻችሁም ሁሉ
ዳግም ፍርድን ሲመረምሩ፡ እዚህ ችሎት ይቀርባሉ
በዚህ መንበር ይዳኛሉ
በዚያን ቀን ፍርድ የሚሰጠው
ከእኔ በብዙ የላቀ፡ እጅጉን አስተዋይ ሰው ነው
ይህን ብሎ ደመደመ ዳኛው ሲያሰናብታቸው።

ሳላዲን	እረ በነቢያችን ! እረ የተአምር ጌታ !

ናትናኤል	እርሶም እንግዲህ ሡልጣን ሆይ
ብልኅ ከሆኑ ኬህ በላይ…

ሳላዲን	(ወደናትናኤል በመቅረብ እስከትርሲቱ ፍጻሜ እጁን እንደያዘ ይቀጥላል)
እኔ ያንን ዳኛ እንድሆን ?
አፈር–ድቤ ነው ዳኝነት !
እኮ እኔ ! እኔ ትቢያው ! እረ ያላህ ያለህ ?!

ናትናኤል ምነው ምን አሰቡ ሡልጣን ?

ሳላዲን ውድ ናትናኤል የዚያ ጻኛ ሺህ ዓመታት እስከዛሬም አላለፉም
የሱ የችሎት ወንበርም ከቶ ለኔ አይታሰብም
ግን ሂድ ይሁን እንቱም
ብቻ ወዳጅነታችን፣ ይቀጥል ያም ቢሆን ይህም

ናትናኤል ሳላዲን ሆይ ከእ እሚሹት፣ ሌላስ ጥያቄ የለም ?

ሳላዲን ኧረ ምንም።

ናትናኤል ምንም ምንም ?

ሳላዲን በእውነት ጥያቄ የለኝም

ናትናኤል እኔ እንዲ ምኞቴ ነበር
ለእርስዎ ውለታ ለመዋል የሚያስችለኝ ዕድል ቢኖር

ሳላዲን ዕድል እስኪገኝ አትቆይ፣ አሁኑኑ ነው መናገር

ናትናኤል ገና ከረጅም መንገዴ መመለሴክ ነው ሡልጣን
በሰው ላይ ያለኝን ዕዳዎን ለበሰብሰብኩን ከቶ እስካሁን
በዚህ ክፉ መጥፎ ጊዜ፣ በጅ ያለ ገንዘብም ቢሆን
ጠንቀኛ ነፍስ ተነስቷል፣ እስኪ ነው መያዝ ጥሬውን
ስለዚህ የት እንደማውል፣ ጨንቆኛል በርካታ ብሬን
ለመጪው ጦርነት ዘመን፣ መቋቋሚያ ቀልጦ እሚሆን
ገንዘብ ባይፈልጉ አይቀሩም፣ ሡልጣን ሆይ ከቶ እርስዎም ቢሆን ?
እርሶ ዘንድ ያኖሩልኛል፣ ደፍሬ ብጠይቅ አሁን !

ሳላዲን (በናትናኤል ላይ አይኖቹን ተክሎ)
አቤት ናትናኤል ! መቼም አልሐፊን አማኘው፣ አታማኘው፣
ልጠይቅ ምኞትም የለኝ
ወይስ ያንተው ጥርጣሬ፣ ግፋ ሰጦታ እንድትሰጠኝ !

ናትናኤል የምን ጥርጣሬ ?

ሳላዲን እሱስ ልጠይቅ አልፈቅድም፣ ግን ይቅርታ ናትናኤል
የደበቅሁት አንዳች ስሜት፣ አለ በውስጤ ተንሳኝል
እናም እውነት ለመናገር፣ ወስኜ ነበረ እኔም…

ናትናኤል ይሄንኑ ለመጠየቅ ?

ሳላዲን እንዴታ !

ናትናኤል ኦ ሞቷላ ነገሩ አሁኑኑ
ከነገሩ ያለኝን ገንዘብ፣ በሙሉም ላመጣው ባልችል
የመምሩ ነው ጥሩ፣ ይሄንን ማወቅ ይገባል
ያውቂታል ያንን ቄስ መምር
የእሱ ዕዳ አለብኝ ክፍር

ሳላዲን ቄሱ ?! መቼም በእርግጥ ናትናኤል
የኔን ቀንደኛ ጠላቶች በወርቅህ ረዳሁ እንዳትል ?

ናትናኤል ዘሳላዲን ሊጋስነት ሕይወቱ የዳነውን ቄስ
እሱን እኮ ነው እምጠቅስ

ሳላዲን ስለምንድን አስታወስከኝ፣ ጥንት የረሳሁትን ሰው ነገር
የት ነው ያለውስ እሱ ? ታውቀዋለህ እንዴ ከምር ?

ናትናኤል በሱ በኩል ያእርሶን ነገር፣ ደግነትዎን እንዳወቅሁ
ወሬም ፍጹም አልደረሰህ ?
በርስዎ ሊጋስነት ምክንያት፣ የተረፈች ነፍሱን ሰጥቶ
ልጄን ከእሳት እንዳወጣት፣ ቢሰሙ ምን ይሉ ኸቶ ?

ሳላዲን ምን! እንደዚያ ያለ ገድል አለው ?
እርግጥ እሚያደርግ ነው እሚመስለው !
ቁርጥ እሱን የሚመስለው ወንድሜኳም ቢሆን ቢገጥመው
ያንተን ልጅ ነብስ ለማዳን እሳት ውስጥ መግባትን አይተው
አሁንም አለ ያ ሰው ?
ቶሎ እዚህ እንድታመጣው
ለእህቴ ስርክ ብዙት ማታ፣ ወንድሜን ስለሚመስለው
በልዚህ ሰው ሳወራላት፣ ለማየት እንደጓጓች ነው
በሞቴ እስቲ ፈልገው
የወንድሜን አምሳያ ሰው፣ እህቴ እንድታየው
አየህ ናትናኤል አስተዋልክ
እንደ ነጠላ ብቸኛ፣ መልክም ሥራ ክብርን ደርጓት
ከሰው ልጅ ፍቅር ብቻ መንጭቶ፣ ቢፈጸም አንድ ቀን ድንገት
ለስንት ጥሩ ተግባራት ፤ መመሰድ ሆኖ ምክንያት
የደግ ምግባር ልጅ ልጆች ፤ በሆ ተባዝ እንደወረት!
ወደኔ አምጣው በሞቴ!

ናትናኤል፡ የሳላዲንን እጅ ሰቆ
እሺ እሄዳለሁኝ አሁን ፤
ለላውም ጉዳይ ሞተ
ይወጣል

ሳላዲን፡ አዬ እህቴ እንድትሰማ፣ እዚህ ባመጣኋት ምነው
በአንደ አፍታ ወደሷ ሄጄ፣ ሁሉን እንድታውቅ ማድረግ ነው
በተቃራኒው በር ይወጣል

Quelle:
Lessing, Gotthold Ephraim. Nathan der Weise [in Amharic translation.]
Translated by Nebiy Mekonnen. Addis Ababa: Goethe Institute, [1993] S. 75-89.



Herausgegeben von der Lessing-Akademie
nach einer Idee von Frau E. Niemann (Wolfenbüttel),
unterstützt durch eine großzügige private Spende.

LESSING AKADEMIE

Lessing-Akademie
Schlossplatz 2 · 38304 Wolfenbüttel
Tel.: (05331) 808-227 · Fax: (05331) 808-248
E-mail: lessingakademie@hab.de · www.lessing-akademie.de

Amharisch